# <u>በህግ አምላክ</u> ?!

(አሥራደው ከፈረንሳይ)

ፍትህ

የአዲስ አበባ ልጅ መሆን ወንጀል ነው ?!

የአዲስ አበባ ልጅ ፡ ጎሳ የለውም፤ መታወቂያው ኢትዮጵያዊነት ነው ።

የአዲስ አበባ ልጅ ፡ የድንበር ክልል የለውም፤ አስተሳሰቡ ድንበር ተሻግሮ ፤ ከአድማስ ባሻገር ነው ።

የአዲስ አበባ ልጅ ፡ የሃይማኖት ልዩነት አይነጣጥለውም፤ አብሮ ወደ ፈጣሪው ይጸልያል ።

የአዲስ አበባ ልጅ ፡ ስስት አያውቅም፤ ያገኘውን አነሰ በዛ አብሮ ይቋደሳል ።

የአዲስ አበባ ልጅ ፡ መለያው የጎሳ ምልክት ሳይሆን፤ ኢትዮጵያዊ ዐላማ ሰንደቁ ነው ።

የአዲስ አበባ ልጅ ፡ ሲጨስ ቀርቶ ገና ሳይለኮስ ስለሚሸተው፤ አደብ ግዛ ይላል ።

የአዲስ አበባ ልጅ ፡ በሾኬ ሲጠልፉት፤ ቀድሞ በሳቅ ይጥላል እንጂ ፡ እንደ እንስሳዋ አይራገጥም ።

የአዲስ አበባ ልጅ ፡ ቋንቋው ፍቅር፤ አነጋገሩ ጉራይማሌ፤ ኑሮው አብሮነት፤ ምኞቱ አንድነት፤ ሠፈሩ አራዳ፤ አገሩ ኢትዮጵያ ነው ። ካልገባችሁ ጠይቁት ይነግራችኋል !!

አለኝ ፍቅር የሚያባባ፤

የከተማው ያ'ዲስ አባ፤

የመርካቶ የፒያሳ፤

የካሳንቺስ መከኒሳ፤

የልደታ የበቅሎ ቤት ፤

የንፋስ ስልክ ቂርቆስ ሰፈር

አራት ኪሎ ገዳም ሰፈር፤

ስድስት ኪሎ አፍንጮ በር ፤

ሽሮ ሜዳ ሰንጋ ተራ ፤

ቦሌ ሰፈር ደሞም ቄራ።

በህግ አምላክ !!

የአራዳ ልጅ መሆን ወንጀል አይደለም !

የአራዳን ልጆች ልቀቁ !!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !!

መስከርም 30 ቀን 2011 ዓ.ም. ( እ.ኤ.አ 10/11/2018 )